# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 41 ግንቦት 8 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ



"ብልፅግና ፓርቲ የኮሮና ቫይረስን ለፖለቲካ መጠቀሚያ እያደረገው ነው፡፡"

ዋሲሁን ተስፋዬ

"ለሁሉም ህብረተሰብ ክፍል የሚበቃ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል አለ ብለን አናምንም"

ሙሉዓለም ተገኘ ወርቅ (ዶ/ር)



# ምርጫውን ለማራዘም ይረዳሉ ተብሎ የሚጠበቁት አማራጮች ሲፈተሹ.....



# ምርጫውን ለማራዘም ይረዳሉ ተብሎ የሚጠበቁት አማራጮች ሲፈተሹ.....

ነፃ ሀሳብ

በሕገ መንግሥት አስተምሮ ውስጥ ሕገመንግሥት የሕግና የፖለቲካ አስተሳሰብ ድቃይ ወጤት ነው የሚለው አስተሳሰብ ስር የሰደደ አስተሳሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም የሕገ መንግሥት አርቃቂዎች ወይም አዘጋጆች በአብዛኛው ሊባል በሚችል ሁኔታ የሕግ ውጤትን አስበው የሚያዘጋጁት ሳይሆን የፖለቲካ ውጤትን አስበው የሚያዘጋጁት ነው፡፡ በሕገ መንግሥት የሚወሰኑት ቅርጸ መንግሥት፣ የግዛት ክፍፍል መርህ፣ የገቢ ክፍፍል መርህ፣ የመንግሥት አካላት አወቃቀር፣ የምርጫ ሥርዓት፣ በመንግሥት አካላት መካከል ያለው የእርስ በርስ ቁጥጥር፣ ሕገ መንግሥቱን የማሻሻያ ምክንያቶች፣ ሥነ ሥርዓቱና ሥልጣኑ ወዘተ... የፖለቲካ ባህሪያቸው የበለጠ ጎልቶ የወጣ ነው፡፡ የእኛም ሕገ መንግሥት ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

አሁን ዓለማችንንም ሆነ አገራችንን ያጠቃው የኮሮና ቫይረስ(COVID-19) ወረርሽኝ አገራትን በስፋት እያጠቃ በመሆኑ፤ የቀጣይ አገር አቅፍ ምርጫም ይህንን ተከተሎ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዝሟል፡፡ይህ ያልተጠበቀ ክስተት (acts of God or force majeure) በመሆኑ አገራት እንደየተጨባጭ ሁኔታቸው የተለያየ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡ ኢትዮጵያም በሽታውን ለመከላከል የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደች ትገኛለች፡፡ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ሲባልም በ2012 ዓ.ም ይካሄዳል ተብሎሲጠበቅ የነበረው ሀገር አቀፍ ምርጫም ተራዝሟል፡፡ የምርጫው መራዘም ተከትሎም በርካታ ሕገ መንግሥታዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች እየተነሱ ይገኛሉ፡፡ የምርጫው መራዘም ተከትሎ የቀረቡት አማራጮች ምን ይመስላሉ?አዋጭስ ናቸው?ምርጫው መራዘሙ የሚያመጣው ውጤትስ ምንድን ነው?የሚለውን በጥቂቱ በዚህ ጽሑፍ ለመዳሰስ ተሞክሯል።

## የምርጫው መራዘምና ውጤቱ

ሕገ መንግሥቱ ምርጫ ሊራዘም ስለሚችልባቸው ሁኔታዎች ምንም ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም፡፡ ከመስከረም መጨረሻ በኋላ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ሊራዘም ስለሚችልበት ሁኔታም የሚለው ነገር የለም፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ




በኋላ የአዋጁ ተፈጻሚነት እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ሊራዘም ስለሚችልበት ሁኔታም ግልጽ ድንጋጌ የለም፡ ፡ የሕገ መንግሥት መሻሻልን በተመለከተም ሕገ መንግሥቱ የማሻሻያ ሥነ ሥርዓት ( amendment procedures) ድንጋጌዎች እንጂ የማሻሻያ ምክንያቶችን (substantive reasons for amendment) አልደነገገም፡፡ ይሁን እንጂ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 58 (2) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ዘመን በመስከረም የመጨረሻው ሳምንት ሰኞ እለት እንደሚጠናቀቅ ደንግጓል ፡፡

በዚህ መሰረት የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን መስከረም መጨረሻ 2013 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግም አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫው የግድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መደረግ አለበት የሚል አቋም ሲራምዱ ታዝበናል ፡፡ ምርጫው ሊደረግ የሚችለው የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከተጠናቀቀ በኋላ ስለሆነ የሥራዘመኑን ያጠናቀቀ መንግሥት ምርጫ ለማካሄድ ሕገ መንግሥቱ ስለማይፈቅድለት የሽግግር መንግሥት ሊቋቋም ይገባል በሚል የሚከራከሩም አሉ፡፡

ለሰፊ ውይይት ይረዳ ዘንድ የቀረቡት አማራጮች እና የሚያቀርቡት መፍትሄ ከዚህ በታች ተብራርቷል።

## 1. ሕገ መንግሥቱን ማሻሻል

ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል የሥነሥርዓትድንጋጌዎች በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 104 እና 105 ላይ ተደንግገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎቹ ውጪ ሕገ መንግሥቱ የማሻሻያ ምክንያቶች በሚል የያዘው ድንጋጌ የለም፡፡ በዚህ መሰረትም አንዳንድ የሕገ መንግሥት ሕግ ምሁራን ሕገ መንግሥቱ ሊሻሻል የሚገባበትን ምክንያት በተመለከተ ምንም ገዳቢ ምክንያት የለም በማለት በጥሩ ጎኑ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ ፡፡ ስለሆነም ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ እንጂ ገዳቢ ድንጋጌ የለም፡፡

እነዚህን የማሻሻያ ሥነ ሥርዓቶች በመጠቀም እንደዚህ ዓይነት ከፍተኛ አገራዊ ቀውስ የሚያስከትሉ ችግሮች ሲከሰቱ ምርጫውን ማራዘምና የምክር ቤቱም የሥራ ዘመኑ ከ....ላልበለጠ የሥራ ዘመን ሊራዘም ይችላል በሚል በአንቀጽ 58 ላይ ማሻሻያ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ማሻሻያ በአንቀጽ 104 እና 105 (2) መሰረት አስፈላጊውን የሁለቱን ምክር ቤቶች 2/3ኛ ድምጽና የክልል ምክር ቤቶችን 2/3ኛ ድምጽ አግኝቶ ተፈጻሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚህ የማሻሻያ ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ ግን ሁለት ቢሆኖችን (scenarios) ማየት ያስፈልጋል፤

1ኛ .ማሻሻያው ይደረግ ቢባል በአንቀጽ 104 መሰረት ህዝባዊ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነና አሁን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሕዝቡ በየቤቱ እንዲሆን እየተመከረ ሕዝባዊ ውይይት ይደረግ ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ነገሮች አሁን ባሉበት ሁኔታ የሚቀጥሉ ከሆነ ጥብቅ የማሻሻያ ሥነ ሥርዓቶችን ተከትሎ ሕገመንግሥቱን ማሻሻል እንደሚከብድ ይታሰባል፡፡ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ሕዝብ ይወያያል እንጂ ሕዝብ ድምጽ ይሰጥበታል (ሕዝበ ውሳኑ ይደረጋል) ስለማይል ውይይቱን ሕዝብ በአካል ሳይሰበሰብ የሚደረግበት አማራጮችን ማየት ለዚህ ችግር መፍትሄ ሊሰጥ እንደሚችል የሚያነሱ ባለሙያዎችም አሉ።

2ኛ .ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 104 መሰረት ሕዝባዊ ውይይት አድርጎ ማሻሻል ካልተቻለ ምክርቤቱ በራሱ ሊወስን የሚችልበት አማራጭ አለወይ የሚለውን ሀሳብም በሁለተኛ ደረጃ መመልከትም ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት ሁለቱ ምክር ቤቶችየሕገ መንግሥት ማሻሻያ ውጤት ያላቸውንና ሕዝብ ያልተወያየባቸውን እንዲሁም ያልታተሙትን የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ውሳኔዎች ማየት በዚሁልምድና ቀዳሚ ውሳኔ (precedence) መሰረት መወሰን ለምን አይቻልም ብሎ ማሰብ ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለቱ ምክር ቤቶች

- የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 103/5 የሕዝብ ቆጠራ በየአስር ዓመቱ መደረግ አለበት በማለት ቢደነግግም አስፈላጊ ሲሆን በሁለቱ ምክር ቤቶች ውሳኔ ሊራዘም ይችላል በሚል ተሻሽሎ ቆጠራው እንዲራዘም ተደርጓል
- የገንዘብ ሚኒስቴር ባቀረበው የሕገመንግሥት ማሻሻያ ጥያቄ (amendment proposal) መሰረትም በአንቀጽ 98 ላይ የተደነገገው የጋራ የታክስና የግብር ሥልጣን በሁለቱ ምክር ቤቶች ውሳኔ የተሻሻለ ሲሆን ሁለቱም ማሻሻያዎች የሕዝብ ውይይት ሳይደረግባቸው፣ ውሳኔዎቹ ሳይታተሙ ተግባራዊ የተደረጉ ናቸው፡፡

በእነዚህ ውሳኔዎች ላይ የምክር ቤቶቹ ውሳኔዎች የሕገመንግሥቱን የማሻሻያ ሥነ ሥርዓት (amendment procedures) የተከተሉ ስላልሆኑ ዋጋ ሊያጡ ይገባል በሚል የቀረበ ቅሬታ የለም፡፡ በመርህ ደረጃ በእንደዚህ ዓይነት የምክር ቤቱ ውሳኔዎች ላይ ውሳኔው ሕገ መንግሥታዊ አይደለም በሚል መቃወሚያ የሚቀርበው ለፍርድ ቤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን መሰል ጉዳይ ለማየት ፍርድ ቤታችን ሥልጣን የለውም፡፡ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን ከሌለው፣ ሕገ መንግሥቱን ለመተርጎም ሥልጣን የተሰጠው (አንቀጽ 62/1) የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከሕዝብተወካዮች ምክር ቤት ጋር አብሮ በጋራ ከወሰነበት የምክር ቤቱ ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ አይደለም የሚለው መቃወሚያ የት ይቀርባል?የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔን እዚህ ጋር የተተወው በመጨረሻ የሚወስነው አካል የፌደሬሽን ምክር ቤት ስለሆነ ስለጉባዔው ሥልጣን መነጋገሩ በውጤት ደረጃ ብዙም ዋጋ የለውም በማለት ነው፡፡ የፓርቲ ሥርዓቱ መሰረታዊ ሚና የሚጫወተው እዚህ ላይ ሲሆን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት የተባለውም ምንያክል በፓርቲው ሥርዓት እንደ ተጠረነፈና ፍርድ ቤትም ሚናው ምን ያክል ተራ የግለሰቦችን ክርክር ብቻ ከማየት ያለፈ ሚና እንደ ሌለው የሚያሳይ ነው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት በዘመናት ሂደት ውስጥ ስር እየሰደደ እስከሚሄድ ድረስ የፓርቲ ሥርዓት ሚና ጉልህ ሆኖ መቆየቱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን የምክር ቤቱ ውሳኔዎችን መሰረት አድርገን ስናስብ አሁንም የምርጫውንና የምክር ቤቱን የሥራ ዘመን መራዘም በተመለከተ ከመወሰን ምን ይከለክለዋል? እነዚህን መሰል ውሳኔዎች የራሳቸውን አከራካሪ ጉዳዮች ቢያስነሱም ወይም ሊያስነሱ ቢችሉም ለጊዜው አካዳሚያዊ ወይም ለአካዳሚያዊ ጉዳዮች ፍጆታ ብቻ ከመዋል ያለፉ አይሆኑም፡፡ በተጨባጭ ካለው ሁኔታ አንፃር ስንገመግመው የተወሰኑ የሕዝብ ተወካዮች ይቃወማሉ ብለን ብናስብ ብልጽግና ፓርቲ ካለው የመቀመጫ ብዛት አንጻር ምክር ቤቱ ከዚህ ቀደምም ተመሳሳይ ውሳኔዎችን የወሰነ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ወዘተ... የሚሉ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ሊወስን ይችላል፡፡

## 2. ከመስከረም በኋላ በስድስት ወር ውስጥ ምርጫ ማካሄድ

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 60 (1) ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ሕገ መንግሥቱ ይህን እንዲያደርግ ሲፈቅድለት ምንም ዓይነት የምክንያት ገደብ በጠቅላይ ሚንስትሩ ላይ አልጣለበትም፡፡ በርግጥ ይህ ድንጋጌ የሥራ ዘመኑን የጨረሰ ምክር ቤትን የሚመለከት ሳይሆን በሥራ ላይ ያለ ምክር ቤት ተበትኖ ምርጫ ማድረግ ቢያስፈልግ በ6 ወር ወስጥ ምርጫ ማድረግን የሚመለከት ነው በሚል የሚከራከሩ አሉ፡፡ በሌላ በኩል በሥራ ላይ እያለ ለምሳሌ በነሐሴ ወር ላይ በ6 ወር ውስጥ ምክር ቤቱ ምርጫ እንዲደረግ ቢወስን ሕገ ወጥ ነው የሚል ትችት እንጂ ሌላ የተለየ ውጤት አይኖርም፡፡ ምክር ቤቱ የሥራ ዘመኑን ከጨረሰ በኋላ ቀጣይ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን በተመለከተ ሕገ መንግሥቱ ግልጽ ድንጋጌ የለውም፡፡

ምክር ቤቱ የአብላጫ ፓርቲ ምክር ቤት ስለሆነና መንግሥት በፓርቲዎች ጣምራ የተመሰረተ ስላልሆነ ከዚህ ጋር ተያይዞ

አድራሻ
ስልክ
+251118592950
ኢሜይል
ethzema@gmail.com
ትዊተር
www.twitter.com/ethzema
ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)
ግንቦት 8 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

▶ የሚነሳ የሕግ ክርክር አይኖርም፡፡ ብልጽግና ፓርቲ አብላጫውን ሲይዝ ሕወሓት አነስተኛ ድምጽ የያዘበት ምክር ቤት ስለሆነ በፓርቲዎች መካከል በቀላሉ ለመቆጣጠር የሚያስቸግር አለመግባባት ይፈጠራል የሚልስጋት የለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የታተሙ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ቃለ ጉባኤዎች መረዳት እንደሚቻለው ይህ አንቀጽ ብዙም ውይይት የተደረገበት ስላልሆነ የሕግ አውጪው ሃሳብ ምን እንደ ነበር በሚገባ ማወቅ አስቸጋሪ ነው ፡፡

ከፍተኛ የመንግሥትን ትኩረት ስለሚፈልግ መንግሥት ጠንክሮ ሊሠራቸው የሚገቡ በርካታ ሥራዎች እንደሚኖሩ አያነጋግርም፡፡ ስለሆነም ምክር ቤቱን በትኖ ደካማ መንግሥት እንዲኖር ማድረግ የሚመከር አይደለም ፡፡

- ምክር ቤቱን መበተን የፖለቲካ ትኩሳቱንም የበለጠ ሊያጋግለው ይችላል፡፡ መንግሥት የፈረሰ ዓይነት ተደርጎ ሊነዛ የሚችለው ፕሮፓጋንዳ፣ ይህን አጋጣሚ አሰፍስፈው የሚጠብቁና የሽግግር መንግሥት

ውሳኔ ሊሰርዘው ይችላል፡፡ በእኛ ሁኔታ ግን ከላይ እንደ ተመለከትነው ፍርድ ቤት የምክር ቤቱን ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊነት መርምሮ ለመወሰን ሥልጣን ስለሌለው የምክር ቤቱን ውሳኔ ሊሰርዝ አይችልም፡፡ ይልቁንም የፌደሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ አማካኝነት በሚቀርቡለት አቤቱታዎች መነሻነት የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ስለሚሽር ሥልጣኑ የተገላቢጦሽ ነው ፡፡
ስለሆነም ፍርድ ቤት የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት (a system

**« ጠቅላይ ሚኒስትሩም ካልፈለገ ምክር ቤቱ አይበተንም፡፡ »**

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምክር ቤቱን መበተን የሚችለው ምክር ቤቱ ከፈቀደ እና እሱም ይህን ማድረግ ከፈለገ ነው ፡፡ ምክር ቤቱ ካልፈቀደና ጠቅላይ ሚኒስትሩም ካልፈለገ ምክር ቤቱ አይበተንም፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምክር ቤቱን የሚበትነው በ6 ወራት ውስጥ ምርጫ ለማካሄድ ሲሆን ምክር ቤቱ ካልፈቀደ መንግሥት በነበረበት ቀጥሎ በ6 ወራት ውስጥ ምርጫ ማካሄድ ስለሚቻል ምክር ቤቱ መበተን አያስፈልገውም፡፡ ምክር ቤቱ ሕግ እያወጣና ጠቅላይ ሚኒስትሩም የአስፈጻሚነት ተግባሩን በመደበኛው ሁኔታ እያከናወነ ሕገ መንግሥታዊ ስርዓቱ እንዲቀጥል ቢደረግ ይመረጣል፡፡ ምክር ቤቱ ፈቅዶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምክር ቤቱን ከበተነ ግን ምርጫው እስከሚካሄድ ድረስ ሕግ ማውጣት አይቻልም ፡፡
ስለሆነም፣

- ምክር ቤቱ ከተበተነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በራሱ ሕግ ማውጣት ስለማይችል አገሪቱ ተመልሳ ቀውስ ውስጥ ብትገባ እንኳን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማውጣትና ችግሮችን መቆጣጠር ስለማይቻል ምክርቤቱን መበተን ጉዳት አለው፣
- ምርጫው የተራዘመው የህዝብ ጤና ላይ ከፍተኛ ስጋትና ጭንቀት በተፈጠረበት ሁኔታ ስለሆነና ይህም በሽታው መፍትሄ ቢያገኝ እንኳን በሽታው ያደረሰው እና የሚያስከትለው ውጤትም ለወደፊቱ

ካልተቋቋመ የሚሉ ፖለቲከኞች ጉዳዩን ከሚገባው በላይ ሊያጦዙት ስለሚችሉ ምክር ቤቱን መበተን የበለጠ ጉዳት አለው ፡፡




የምክር ቤቱ ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ አይደለም ቢባል ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን ማየትም ያስፈልጋል፡፡ የምክር ቤቱን ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ አይደለም በማለት ለመወሰን የሚችለው ፍርድ ቤት ወይም ሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤት በሆነባቸው አገራት፤ ለምሳሌ አሜሪካ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ጀርመን፣ የኬንያ ፍርድ ቤትምወዘተ. ፍርድ ቤቱ የምክር ቤቱን

of check and balance) የለንም ፡፡ ፍርድ ቤት ይህን ዓይነት የምክር ቤት ውሳኔ መሰረዝ በማይችልባቸው አገራት በአብዛኛው የፓርቲ ሥርዓቱ የምክር ቤቱን ውሳኔ መፈታተን ስለማይችል የምክር ቤቱ ውሳኔ ያለምንም ችግር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በርግጥ የእርስ በርስ ቁጥጥር ባለባቸው አገራትም ቢሆን የፓርቲ ሥርዓት የሚጫወተው ሚናቀላል አይደለም፡፡ ስለሆነም የእኛም ነባራዊ ሁኔታ ከዚህ የተለየ ስላልሆነ የፓርቲ ሥርዓታችን የምክር ቤቱን ውሳኔ በቀላሉ ለማስፈጸም የሚመች ነው፡፡
ለ6 ወር በማራዘሙና ሕገ መንግሥቱን በማሻሻሉ መካከል የውሳኔው መሰረታዊ ምክንያት የሚሆነው የበሽታው የመራዘምና በአጭር ጊዜ ውስጥ በቁጥጥር ስር የመዋል እውነታ ነው፡፡ ወረርሽኙ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቁጥጥር ስር የሚውል ከሆነ የ6 ወር ማራዘሚያ ሥርዓትን መጠቀም ይመከራል፡፡ በሽታው እየከፋ ከሄደ ግን የሕገ መንግሥት ማሻሻያ መጠቀም ይመከራል ፡፡

## 3. የአስቸኳይጊዜአዋጅ

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አንዱ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መኖር ከዚህ በኋላ በሚኖረው የበሽታው አስከፊነት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ▶



▶ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ የሚቆይበት ሕገ መንግሥታዊ መሰረት ስለሌለ ዞሮ ዞሮ ምክር ቤቱ ከመስከረም በኋላ ሥራውን መቀጠሉ ሕገ ወጥ ነው የሚል መቃወሚያ መቅረቡ አይቀርም፡፡

በርግጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እስከሚያልቅ ድረስ የምክር ቤቱና የአስፈጻሚው የሥራ ዘመን ሊቀጥል ይችላል፣ ሕገ መንግሥቱም በዚህ መልክ ነው የተቀረጸው ብለው የሚከራከሩቢ ኖሩም ይሕን በግልጽ የሚደግፍ ማስረጃና ተጨማሪ ድንጋጌ ግን የለም፡፡ የሕገመንግሥት ድንጋጌ ይቅርና ሌላም ሕግ ቢሆን በደፈናው አይተረጎምም፡፡ በሽታው የበለጠ እየከፋ ከሄደ በአንቀጽ 93 መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ አስፈላጊ የሚሆነው ሕገ መንግሥቱን በመጀመሪያው አማራጭ ከማሻሻል ጋር ነው፡፡

## 4. የሕገ መንግሥት ትርጉም

አስካሁን በነበረው የሕገ-መንገስት ትርጉም ልምድ (the practice of constitutional interpretations) ሕገ-መንግስቱ

- ከክልሎች በቀረበ ጥያቄ
- ከግለሰቦች በቀረበ ጥያቄ
- በፍርድ ቤቶች በቀረበ ጥያቄ የተነሳ ወዘተ፤

**«የሕገ-መንገስት ትርጉም በሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ በኩል አስተያየት ቀርቦ በፌደሬሽን ምክር ቤት በኩል ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን በርካታ ጥያቄዎች ደግሞ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልጋቸውም በሚል ውድቅ ተደርገዋል። የተወሰኑ ውሳኔዎችም ታትመዋል። እንደ አሁኑ የምርጫ መራዘም ጉዳይ ሕገመንግሥቱ ያልሸፈነው ጉዳይ ነው በሚል የተሰጠ ትርጉም ግን አላጋጠመም (ከታተሙት ውስጥ)።»**

የሕገ-መንገስት ትርጉም በሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ በኩል አስተያየት ቀርቦ በፌደሬሽን ምክር ቤት በኩል ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን በርካታ ጥያቄዎች ደግሞ የሕገመንግሥት ትርጉም አያስፈልጋቸውም በሚል ውድቅ ተደርገዋል። የተወሰኑ ውሳኔዎችም ታትመዋል። እንደ አሁኑ የምርጫ መራዘም ጉዳይ ሕገመንግሥቱ ያልሸፈነው ጉዳይ ነው በሚል የተሰጠ ትርጉም ግን አላጋጠመም (ከታተሙት ውስጥ)።እስካሁን የሚቀርቡት ጥያቄዎች የሕገ መንገሥት ክርክርን (constitutional disputes) እና የሕገ መንገሥት ትርጉም ጥያቄዎችን (constitutional interpretations) መሰረት ያደረጉ ናቸው። ሁለቱም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62 (1) መሰረት የፌደሬሽን ምክር ቤቱ ሥልጣኖች ናቸው። በዚህ መሰረት የሕገ መንገስት ትርጉም የዳበረ ነው ባይባልም የሕገ መንግሥታዊ ሕጉና ፖለቲካው አካል እየሆነ የመጣ ለመሆኑ ግን አያከራክርም። ይሁን እንጂ ውሳኔዎቹ አጭርና በሚገባ ምርምር ተደርጎባቸው የሚሰጡ ስላልሆኑ ለአገራችን የሕገ መንግሥት ትርጉም እሳቤዎች (thoughts on constitutional interpretations) እድገት አስተዋፆ እያደረጉ አይደለም። በዚህ የተነሳ የሕገመንግሥት ትርጉሞቹ በምንዓይነት መርህ ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ በቀላሉ ለማወቅ የሚቻልባቸው አይደሉም።

ሕገ መንግሥቱን የሚተረጉመው አካል የፖለቲካ ተጽዕኖ ያለውና የፖለቲካ አካሉ አንዱ ክፍል ነው የሚለውን ትችት በተመለከተ አሁን ካለው አገራዊ አጣብቂኝ አንጻር እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሊታይ የሚችል ነው። ለወደፊቱ የሕገ መንግስት ማሻሻያ ሲደረግ አብሮ የሚታይ እንጂ በዚህ ደረጃ ግን ሕገ መንግስታዊ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም።
የሕገ መንግሥት ትርጉም ምን ዓይነት ውጤት እንደሚኖረው ጉባዔው ምክረ ሃሳቡን ለፌደሬሽን ምክር ቤት እስኪያቀርብ ድረስ ይሄ ነው ብሎ መናገር አይቻልም። በሀገር ደረጃ የገባንበትን ትልቅ አጣብቂኝ ውጤቱ በእርግጠኝነት ለማይታወቅ ሂደት አሳልፎ መስጠት የጉዳዩን ክብደት በሚገባ ያልተረዳ ውሳኔ ነው የሚል መከራከሪያ ይቀርብበታል። በትርጉም የሚሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ የመነጬት ሌሎች አማራጮች መካከል አንደኛውን መንግሥት እንዲተገብር የሚፈቅድ ከሆነም ለሕገ መንግሥት ትርጉም የሚውለው ጊዜ እና ሀብት ትርጉም የለሽ ሊያደርገው ይችላል።

# ቅኝት

## ምርጫ ወረዳ 24ን በወፍ በረር

በዛሬው የቅኝት አምዳችን ስር ምርጫ ወረዳ 24ን እንቃኛለን፡፡ ምርጫ ወረዳ 24 በሥሩ ልዩ ወረዳ ተብሎ የሚጠራውን ልደታን ጨምሮ 11 ወረዳዎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን በሥሩም 249 የምርጫ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ ወረዳው በአሁኑ ሰዓት ከ300 በላይ አባላት አሉት፡፡ ምርጫ ወረዳው አየር ጤና መገርቱ ሕንፃ አንደኛ ፎቅ ላይ ቢሮውን ከፍቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

በዛሬው የቅኝት አምዳችን ምርጫ ወረዳ 24ን በጨረፍታ እንመለከታለን፡፡ ምርጫ ወረዳውን በሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ ያቀበሉንን የምርጫ ወረዳው ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊን በአንባቢዎቻችን ስም እናመሰግናለን፡፡




### ምርጫ ወረዳ 24 ሥራ አስፈፃሚ መችና እንዴት ተዋቀረ?

የምርጫ ወረዳ 24 ሥራ አስፈፃሚ ኢዜማ በተመሰረተ በ15ኛ ቀኑ ቢሮውን ከፍቶ እንቅስቃሴ እንደጀመረ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ያስረዳሉ፡፡ ኃላፊው ከዓመት በፊት ምርጫ ወረዳቸውን ሲያቋቁሙ የገጠማቸውን ፈተና ወደኋላ መለስ ብለው ሲያስታውሱ መጀመሪያ አካባቢ አባላትን በመመልመል በኩል ችግር ገጥሟቸው እንደነበርና 15 አባላትን ብቻ ይዘው እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ያወሳሉ፡፡ በሂደት ግን ይህን ችግር መቅረፍ እንደቻሉና በአሁኑ ሰአት በአግባቡ ወርሃዊ የአባልነት መዋጮዋቸውን የሚከፍሉ ከ300 በላይ አባላት እንዳላቸው ኃላፊው ይገልፃሉ፡፡ ወረዳው 10 የሥራ አስፈፃሚ አባላትን የያዘ ሲሆን በተጨማሪነትም የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ፣ የሕግና ዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ አሉት፡፡ እያንዳንዱ ኮሚቴ ከዋናው የፓርቲው መተዳደሪያ ደምብ ጋር በማይፃረር መልኩ የተነደፈ የውስጥ ደምብ እንዳለው ኃላፊው ያስረዳሉ፡፡ የውስጥ ደምቦቹም ለወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ የፀደቁ መሆናቸውን በወረዳው ሥራ አስፈፃሚ አባላትና በወረዳው አባላት መካከል መናበብ እንዳለ ኃላፊው ይናገራሉ፡፡

### በምርጫ ወረዳው ያለው የሴቶች ተሳትፎ ምን ይመስላል?

ወረዳችን በሴቶች ተሳትፎ ላይ የማያወላውል አቋም አለው የሚሉት ኃላፊው የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ሲባል እያንዳንዱ አባል ሴቶች ምርጫ ወረዳውን እንዲቀላቀሉ ግፊት እንደሚያደርግ ይናገራሉ፡፡ በአጠቃላይ በወረዳቸው ከሚገኙ 300 በላይ አባላት መሀል በአሁኑ ሰአት 35 ያሕሉ ሴቶች መሆናቸውን ኃላፊው ገልፀዋል፡፡ በሥራ አስፈፃሚ ደረጃም በወረዳው ሁለት ሴት ሥራ አስፈፃሚ አባላት አሉ፡፡ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ እና የሙያ ማኅበራት ተጠሪዎች ሴቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በወረዳው የአስመራጭ ኮሚቴዎች ውስጥም ሴቶች እንዳሉ ሕ/ግንኙነት ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡ ይህ ቁጥር ግን በጣም ትንሽ ነው ብለው እንደሚያምኑና ከዚህም በላይ ሴቶችን ማሳተፍ እንደሚያስፈልግ በአፅንኦት ይናገራሉ፡፡ ‹‹ሴት ልጅን ማበረታታት ማለት ማኅበረሰብን ማበረታት ነው ይባላል›› የሚሉት ኃላፊው በቀጣይነትም የሴቶችን ተሳትፎ ለማጎልበት አቅደው እንደሚንቀሳቀሱ አስረድተዋል፡፡

### የምርጫ ወረዳው ጥንካሬ ምንድን ነው?

ምርጫ ወረዳው በዋናነት የሚወሳው ሥራው የበጎ አድራጎት ስራው ነው፡፡ በፖለቲካ ቀውስ የተነሳ ለተፈናቀሉ ዜጎች በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት በተዘጋጀ የቁሳቁስ ማሰባሰቢያ መርሃግብር ላይ በመገኘት ወደ 60ሺህ ብር የሚጠጋ ቁሳቁስና አልባሳት ድጋፍ ማድረጋቸውን ኃላፊው ያስረዳሉ፡፡ በዶክተር ካትሊን ሀምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል በመገኘትም የንፅህና መጠበቂያ እቃዎችን በመስጠት ድጋፍ ማድረጋቸውን ኃላፊው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪነትም ባለፈው አንድ ዓመት የወረዳውን አባላት በማስተባበር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ደም ባንክ በመገኘት ለሶስት ጊዜያት ያሕል የደም ልገሳ ማድረጋቸውን ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

ከአባላት መፅሀፍትን በማሰባሰብም ▶




በቢሯቸው ውስጥ ቤተመፅሀፍት ማቋቋማቸውን ኃላፊው ይናገራሉ፡፡ ሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ የሚመራው ግብረሀይል እንዳለና ግብረሀይሉ መፅሀፍ የማሰባሰብ ሥራዎችን እንደሚሰራና ያሰባሰባቸውን መፅሐፍት አባላት ከቤተመፅሀፍቱ በውሰት በመውሰድ እንዲያነቡት በማድረግ የንባብ ባሕላቸውን እንዲያሳድጉና የእውቀት አድማሳቸውን እንዲያሰፉ እገዛ እያደረጉ እንዳሉ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው አብራርተዋል፡፡

ምርጫ ወረዳ 24 ከተቋቋመ በኋላ በሥሩ በሚገኙት 10ሩም ወረዳዎች ራሱን እንዳስተዋወቀና ወረዳ 23፣ 21፣ 25 እና 22 እንዲቋቋሙ ድጋፍ ማድረጉን ኃላፊው ይገልፃሉ፡፡ የኮሮና ወረርሽኝን በመከላከል ረገድም ከወረዳ 1/9 ጋር በመሆን ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መስራታቸውን ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡ ከዚሁ ከኮሮና ቫይረስ ጋር በተያያዘ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው በወረዳቸው ለሚገኙ አቅመ ደካማ ለሆኑ ነዋሪዎች የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና እህል ማበርከታቸውን ኃላፊው ገልፀዋል፡፡ በሥራቸው በሚገኙ 10ሩም ወረዳዎች ላይም የኮሮና ቫይረስን በሚመለከት የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ነድፈው ስለ ቫይረሱ ግንዛቤ ማስጨበጣቸውን እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደም ባንክ ወረርሽኙን ተከትሎ የተፈጠረበትን የደም እጥረት ለመቅረፍ ላቀረበው ጥሪ ወረዳቸው የደም ልገሳ በማድረግ አዎንታዊ ምላሽ መስጠቱን ኃላፊው ያወሳሉ፡፡

### የኢዜማን ራዕይ፣ ተልዕኮና ግብ ለምርጫ ወረዳው ነዋሪዎችና አባላት ከማስተዋወቅ አንፃር ምርጫ ወረዳው ምንያሕል ሥራ ሰርቷል?

የኢዜማ ራዕይ፣ ተልዕኮና ግብ ለማስተዋወቅ በምርጫ ወረዳቸው ቢሮ ውስጥ ይህንን የሚያስረዱ የተለያዩ ሰነዶች እንዳሉና ሰነዶቹን የትኛውም አባል በቀላሉ ቢሮ በመምጣት ሊያገኛቸው እንደሚችል ኃላፊው ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ሲባል በቋሚ ሰራተኝነት የምታገለግል ፀሀፊን መቅጠራቸውን ገልፀዋል፡፡ ፀሀፊዋ የሙሉ ጊዜ ሰራተኛ ስትሆን የኢዜማ ራዕይ፣ ተልዕኮና ግብ የሚያስረዱ ሰነዶችን ፈልጎ ለሚመጣ ሰው የምትሰጥ መሆኗን ኃላፊው አብራርተዋል፡፡

ኢዜማን በህዝብ ተወካዮች ም/ቤትም ሆነ በአዲስ አበባ ም/ቤት በተሻለ ሊወክሉ የሚችሉ ተወዳዳሪዎችን ለመመልመል ምን አድርጋችኋል?

በወረዳው የሚገኘው የእጩዎች አስመራጭ ኮሚቴ መዋቀሩንና ኮሚቴው ከተዋቀረ ጀምሮ 15 ያሕል ተመራጮችን ማግኘት መቻላቸውንና የምርጫውን መራዘም ተከትሎ በእጩነት መቅረብ ለሚፈልጉ ሰዎች ወረዳቸው በሩን አሁንም ድረስ ክፍት ማድረጉን ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ያስረዳሉ፡፡ የእጩዎቹ የፆታ ተዋስኦ፣ እድሜና የትምሕርት ደረጃ የተመጣጠነ መሆኑን ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡ ለእጩነት በወረዳቸው ከተመዘገቡት 15 ሰዎች መህልም 7ቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ም/ቤት ለመወዳደር ማመልከቻ ሲያስገቡ የተቀሩት 8ቱ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እጩ ሆኖ ለመቅረብ ማመልከቻ አስገብተዋል፡፡

እንደ መውጫ

ምርጫ ወረዳ 24 ማኅበረሰብ ከፍተኛ የሆነ የነፃነትና የፍትሕ ናፍቆት አለበት የሚሉት የምርጫ ወረዳው ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ወረዳቸው ለነፃነትና ለፍትሕ ምንያሕል ቀናኢ እንደሆነ በምርጫ 97 ወቅት ማረጋገጡን ያወሳሉ፡፡ የምርጫ ወረዳው ነዋሪዎች ራሳቸው በፈለጉትና በመረጧቸው አስተዳዳሪዎቹ እንዲተዳደሩ እንደሚፈልጉና ለዚህም ሲሉ በትጋት እንደሚሰሩ ኃላፊው ይናገራሉ፡፡

# ቆይታ

## «የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ከሚደረግ እንቅስቃሴ ተቆጥበው እንደሰለጠነ እና ለህዝብ አደራ እንደተቀበለ ተቋም ለህዝብ በሚጠቅሙ አካሄዶች ላይ ብቻ ሊንቀሳቀሱ ይገባቸዋል»

ዶ/ር ቃልኪዳን በኃይሉ በሙያዋ ጠቅላላ ሐኪም (General Physician) ናት፡፡ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ጤና ፖሊስ ቡድን አባልም ናት፡፡ ስለ ኮሮና ቫይረስና ከቫይረሱ ጋር በተገናኘ ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ዜጎች መድረክ ላነሳቻቸው ጥያቄዎች ሙያዊ ማብራሪያ ሰጥታለች፡ ዶ/ር ቃልኪዳን በኃይሉ ጊዜዋን ሰውታ ለጥያቄዎቻችን ምላሽ በመስጠቷ በአንባቢዎቻችን ስም ጥልቅ ምስጋና እናቀርባለን ፡፡ መልካም ንባብ!



**በሀገራችን በኮሮና ቫይረስ የተያዙ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ይገኛል፡፡ ቫይረሱን በማኅበረሰቡ ውስጥ የስርጭት አድማሱን እንዳያሰፋ ምን መደረግ አለበት?**

ያለን የአኗኗር ዘይቤ እና ማህበረሰባዊ ቁርኝት የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመግታት እንደ ማህበረሰብ የምናደርገው ጥረት ፈታኝ ያደርገዋል። የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የእያንዳንዱ ዜጋ ሲልም የማህበረሰባችን እና የመንግስት ሚናና ሃላፊነት ወሳኝ እና ተመጋጋቢ ነው። ማህበረሰባችን ላይ ያሉ የተለያዩ የተሳሳቱ አመለካከቶች መወገድ አለባቸው። ለምሳሌ እስካሁን ምንም ካልሆንን ከዚህ በኋላ ምንም አንሆንም በሚል የሚታዩ የአቋም እና የጥንቃቄ መዋዠቅ እንዲሁም በአገር ደረጃ ሪፖርት የሚደረገው የታማሚ ቁጥር ሲጨምር መደናገጥና ጥንቃቄ ማድረግ፣ ከቀናት በኋላ ደሞ ወረርሽኙ እንዳልተከሰተ መዘናጋት፣ ,ሪፖርት የሚደረጉ ቁጥሮች ለይቶ ማቆያ ካሉት ውስጥ እንጂ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ስርጭት እንደማያሳይ በመረዳት አለመዘናጋት፣, ኢትዮጵያ የእምነት አገር ናት ምንም አንሆንም ሌሎች አገሮች ወረርሽኙ የተስፋፋው በፈጣሪ ቁጣ ነው ከሚል የተሳሳተ አመለካከት በመውጣት የጤና ባለሙያዎችን ምክርና የመንግስትን ትእዛዝ በሚገባ መፈፀም አስፈላጊ ነው፡፡

**በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ወረርሽኙን ለመቆጣጠር በብዛት እየተተገበረ ያለው ከውጪ የሚመጡ ሰዎችን ለይቶ ማቆያ ማስገባትና በየቀኑ ምርመራ ማካሄድ ነው፡፡ ከዚህ በዘለለ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ምን መደረግ አለበት?**

ማንኛውም የሳንባ ምች ያለው ሰው የኮሮና ምርመራ እንዲደረግለት ማድረግ፡፡_ከጎረቤት አገራት በየብስ ትራንስፖርት ወደአገራችን የሚገቡ እና የጉዞ ወይንም ከታመመ ሰው ጋር ንክኪ ሳይኖራቸው በበሽታው የሚጠቁ ሰዎች ቁጥር መጨመር የመከላከል ስልታችንን መፈተሽ እንዳለብን ያሳያል።ስለሆነም ድንበር አካባቢ በተለይም ከጅቡቲ፣ አፋር፣ ድሬዳዋ፣, ከኬንያ ሞያሌ ,በሶማሌ እና ሌሎችም ከፍተኛ የንግድ፣ የኮንትሮባንድ እና ከፍተኛ የሰው ፍሰት የሚስተዋልባቸው መስመሮች ላይ ማህበረሰቡን የማንቃት በድንበር አካባቢ ያለውን የሰው ፍሰት መቆጣጠር እና የመገደብ ሥራዎችን መከወን ግድ ይላል፡፡ ክልሎች ጥለውት የነበረውን ከክልል ክልል ከከተማ ከተማ የመንቀሳቀስ ገደብ ከማላላት ይልቅ አጠናክሮ በመቀጠል በሽታው ከትላልቅ ከተሞች ወደ አብዛኛውን ህዝብ ወዳቀፈው የገጠሪቱ የአገር ክፍል እንዳይሰራጭ መግታት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪነትም መንግሥት ያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በእምነት ቦታዎች ላይ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ቦታ ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ቁርጠኛ አቋም ሊኖረውና ይገባል ፡፡

**ቫይረሱ የሚታወቁ ምልክቶች ቢኖሩትም ሁሉም ምልክቶች ግን በታማሚ ላይ ላይታዩ እንደሚችሉ ሲገለፅ ይሰማል፡፡ ለምሳሌ አንዳንዱ ታማሚ ደረቅ ሳል ብቻ ሲታይበት ሌሎች ምልክቶች ግን ላይታዩበት ይችላሉ፡፡ በአንፃሩ አንዳንዶች ላይ ደግሞ ከተገለፀው የደረቅ ሳል፣ ትኩሳት፣ ትንፋሽ ማጠርና የጉሮሮ ሕመም በተጨማሪ የማስቀመጥ ምልክቶችም እንደታዩ ሲገለፅ ነበር፡፡ ቫይረሱ ከሰው ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶች አንድ ያልሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው?**

የበሽታው ምልክቶች ከሰው ሰው የሚለያዩበት ምክንያት የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም ከሰው ሰው ከእድሜ እድሜ ስለሚለያይ እና ጠንካራ የመከላከል አቅም ያለው ሰው ምንም ምልክት ሳያሳይ ወይንም ቀላል ምልክቶች ብቻ ኖረውት ሊያገግም ይችላል።,የምንጠቃበት የቫይረስ መጠን ስለሚለያይ,የምንመረመርበት ወቅት ስለሚለያይ ለምሳሌ ገና ምልክት ሳይሰጥ በሚራባበት ወቅት ነው (incubation period ) ወይስ ገና ቀላልና ጠቅለል ያለ ምልክት (ድካም ራስ ምታት) መስጠት በሚጀምርበት ወቅት ነው ወይስ የከፋ ▶ ጉዳት (የመተንፈስ መቸገር )ባስከሰተ ጊዜ ነው,ሌላው ደሞ ቫይረሱ በሽታ ለማምጣት ሰውነት ውሰጥ የሚያካሄደው ስልት (pathogenesis) ሰፊና የተለያየ የሰውነት ክፍልን ስለሚያጠቃ ምልክቶቹም ከሰው ሰው የተለያየ ሆኗል ሳንባው የተጠቃ ሰው አየር ማጠር ሳል ለመተንፈስ መቸገር ሲገጥመው የአንጀት ቱቦ የመጀመሪያ ሽፋን (mucosal epithelium ) የተጠቃ ሰው ቀለል ያለ ተቅማጥ ሊኖረው ይችላል።የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንዲሁም የታካሚዎች ሁኔታ ቫይረሱ የደም መርጋት መቅጠን ሲስተምን በማዛባት የደም መርጋትና ከመርጋት ጋር ተያያዥነት ላላቸው ውስብስብ ችግሮች እንደሚዳርግ ያሳያሉ።

**በቫይረሱ የተያዘ ሰው አገግሞ በድጋሚ በቫይረሱ ሲያዝ የሰውነቱ የነጭ ደም ሴሎች ቫይረሱን የመከላከል ብቃታቸው ላይ የሚያሳድረው ጉዳት አይኖርም? ተጠቂውስ በድጋሚ በመያዙ ለምን አይነት አደጋ ይዳረጋል?**

ቫይረሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያጠቃ በተጠቁ ሴሎች የሚመረተውና የቫይረሱን በሰውነት ውስጥ የመራባት መጠን እንዲቀንስ የሚያደርገው ኢንተርፌሮን የተባለ ፕሮቲን ቫይረሶቹ በእጅጉ እንዲቀንስ ያደርጋል ከዚህ በተጨማሪም ከነጭ ሴሎቻችን የሚወጡ ሌሎች ኬሚካሎች በከፍተኛ መጠን እና ተገቢ ባሎነ ሁኔታ መጠናቸው እነዲጨምርና የራሳችን በስታን የመከላከል ስይስተማችን የራሳችንን ሰውነት እንደጠላት በመቁጠር ከፍተኛ ቁስል(ኢንፍላሜሽን) እንዲከሰት ያደርጋል። በ ቢ ሊምፎሳይት ተብለው በሚጠሩ የነጭ የደም ሴሎችየሚመረቱት አንቲቦዲ የተባለው ኬሚካል ቫይረሱን ለማውደም የሚጠቅም ሲሆን አንድ ሰው በድጋሚ ቫይረሱ ሊያጠቃው ቢፈልግ ይሄ ኬሚካል ቫይረሱን ስለሚያስታውሰው በድጋሚ የመጠቃት እድላችን እንዲጠብ ያደርገዋል።ነገር ግን ድጋሚ ያለመጠቃት እድላችን እስከመቼ ድረስ ነው የሚለውና እነዚህ አንቲቦዲዎች በሽታውን እስከወዲያኛው ደግሞ እንዳይዘን ለማድረግ ምን ያክል ጠንካራ ናቸቸው የሚለው ገና ጥናት ላይ ነው። በድጋሚ በቫይረስ ስንጠቃ ነገሮች የመሻሻል እንጂ ከመጀመሪያው የመባባስ ሁኔታ አያሳዩም።

**እንደሌሎች ቫይረሶች ሰውነታችን በዚህ ቫይረስ ከተጠቃ በኋላ መልሶ ሲያዝ የመከላከል አቅሙን ሊያዳብር የማይችለው በምን የተነሳ ነው?**

ቫይረሶች ዝርያቸውና ቅርፃቸቸው በጣም የሚለያይ ሲሆን አንዳንዶቹ አንድ አይነት ቅርፅ ብቻ ያላቸውና እራሳቸውን ቶሎ ቶሎ ስለማይቀይሩ አንዴ ካጠቁን በኋላ ሰውነታችን በደንብ ስለሚያቃቸው መልሰን በነዛ ቫይረሶች አንጠቃም።እንደነ ኮሮና ያሉ ቫይረሶች ደግሞ ብዙ አይነት ቅርፅ ስላላቸውና ቶሎቶሎ ራሳቸውን ስለሚቀይሩ በተቀየረው ቫይረስ ድጋሚ ብንጠቃ ከዚ ቀደም የተመረተው አንቲቦዲ ስለማያቃቸው የእድሜ ዘመን ወይንም የረጅም ጊዜ በድጋሚ ያለመጠቃት ዋስትና እንዳይኖረን ያደርጋል።

**የኢትዮጵያ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ይፋ ያደረገውን አህዝ ከተመለከትን እስካሁን በሀገራችን በቫይረሱ በብዛት የተያዙት ወጣቶች ናቸው፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?**

በኮሮና ቫይረስ ከተጠቁ በኋላ ለከፋ ጉዳት የሚዳረጉት በእድሜ የገፉና ተጓዳኝ የጤና እክል ያላቸው ሰዋች ቢሆኑም በቫይረሱ ለመጠቃት ሁሉም የእድሜ ክልል እኩል ነው። በአገራችን የተጠቂዎች ቁጥር ወጣት መሆን አንድም ወጣቶች በስራም ይሁን በሌላ ምክንያት ከቦታቦታ ተንቀሳቃሽ ስለሆነ ተጋላጭነታቸውን ያሰፋዋል። ከዚህ በተጨማሪም በአገራችን ወጣቱ ከፍተኛውን የህዝብ ብዛት ቁጥር ስለሚይዝ ነው ።

**መንግሥት የሚከተለው የጤና ፖሊሲ መሰል ወረርሽኞችን ከመከላከል አንፃር እንዴት ይታያል?**

መንግስት እየተከተለ ያለው መከላከልን መሠረት ያደረገ የጤና ፖሊሲ ቢሆንም በተደጋጋሚ እየተከሰቱ ያሉ እንደ ኮሌራ፣ ቢጫ ወባ፣ ,ቺኩንጉንያ፣ ዳንጉ ፌቨርና ሌሎችም እንዲሁም አሁን ላይ የተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ ብዙ ክፍተቶች እንዳሉብን ማሳያ ናቸው። የጤና ፖሊሲው ከወረቀት በዘለለ ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ተቀናጅቶ ሲሰራበት የወረርሽኝ ቅድመ ጥንቃቄ ተብሎ (አካባቢያዊ ጥናት አድርጎ ሊመጣ ያለን አደጋ መተንበይ እና እንዳይከሰት መከላከል ወረርሽኝ ሲከሰት ቶሎ ማወቅና ጥልቀቱን መረዳት ከዛ በኋላ ደግሞ ወረርሽኙን ለመመከት ያለ ብቃት እና ዝግጅት ሲሆኑ) ወረርሽኙ ሲከሰት የሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ጊዜያዊ ግብረ ሃይል ሳይሆን ራሱን የቻለ ተጠሪ ኖሮትና በተዋረድ ከላይ ጀምሮ እስከ ጤና ተቋማት ድረስ ዘላቂ ሲስተም ተዘርግቶለትና የአደጋ እና ወረርሽኝ ተገቢ በጀት ተመድቦ ከፍተኛ የቅድመ ጥንቃቄ ስራ ሲሰራበት አይታይም፡፡

**በኮሮና ቫይረስ የሚጠቁ ሰዎችን ለማከም ሀገራችን በቂና አስተማማኝ የህክምና ቁሳቁስ አቅርቦት (ማስክ፣ የእጅ ጓንት....) አለ? በተለያዩ ክልሎች የህክምና አቅርቦት (ግላቭ፣ ማስክ....) እንደሌለ ባለሙያዎች ሲገልፁ ይሰማል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?**

የመከላከያ ቁሶች እጥረት በአለም አቀፍ ደረጃ ያደጉ አገራቶች ላይ ጨምሮ የተከሰተ ሲሆን አገራችን ላይ ደግሞ ከወረርሽኙም በፊት እጥረት ያለ ስለሆነ አሁን ላይ የአቅርቦት እጥረቱ ተባብሶዋል። ገና ወረርሽኙ ሳይስፋፋ ያሉን ትንሽ ግብአቶች በማለቅ ላይ ናቸው። ይህን ችግር ለመቅረፍ መንግስት በእርዳታ እንዲሁም በብድር ያገኘውንና የኮሮናን ወረርሽኝ ለመግታት የበጀተውን በጀት ኮሮና ወረርሽኝ ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲውል በማድረግ አገር ውስጥ የማይመረቱትን አቅርቦቶች ከውጭ ማስገባትና ከተለያዩ የአገር ውስጥ  አምራች ድርጅቶች ጋር በመነጋገር እዚህ አገር ሊመረቱ የሚችሉ አቅርቦቶችን በበቂ ሁኔታ እንዲመረቱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**ጡረታ የወጡ የህክምና ባለሙያዎች ግዳጅ ላይ ሊሰማሩ እንደሚችል መንግስት ከዚህ ቀደም ገልጿል፡፡ ኮሮና ደግሞ የህክምና ባለሙያዎችን ጭምር በሰፊው እያጠቃ ከመገኘቱ አንጻር ጡረታ ላይ የነበሩ በእድሜ የገፉ ሰዎች ወደ ግዳጅ ሲወጡ ከአድሜያቸው አኳያ በቫይረሱ ለመጠቃትና በቫይረሱ ለመያዝ ከሌላው በተለየ ቅርብ አይሆኑም?**

ጡረታ የወጡ የጤና ባለሙያዎች እንደማንኛውም በእድሜ የገፋ ሰው በበሽታው ከተያዙ ለከፋ ጉዳት የመዳረግ እድላቸው የሰፋ ነው።በተለይም ለግዳጅ ሲጠሩ ተጋላጭነታቸው የሰፋ ያደርገዋል። ነገር ግን እንደዚ አይነት ወረርሽኝ ሲከሰት አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ስለሚያጠቃና ከፍተኛ የጤና ባለሙያ እጥረት መከሰቱ አይቀሬ ስለሆነ ሁሉንም ጤና ባለሙያ ለግዳጅ መጥራትና ማሳተፍ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው።

**የህክምና ተቋማት አካባቢ እና የጤና ባለሙያዎች ሆስፒታል የገቡ ታካሚዎች ምን እየወሰዱ እንዳለ መረጃው ቢኖራቸውም ሰፊው ማህበረሰብ ግን የትኞቹን መድሃኒቶች ኢትዮጵያ እንደምትጠቀም ታካሚዎች ላይ ያመጡት ውጤት እና ለምን እነዛ መድሃኒቶች ተመረጡ የተጠና ጥናትስ አለ ወይ የሚለውን መረጃ የሚነግረው አላገኘም ይህም ልክ እንደከዚህ ቀደም ሁሉ መረጃን የማፈንና ለህዝብ ያለማድረስ የመንግስትን አባዜ ያሳያል። አንድ ሰው ራሱን በቤቱ ውስጥ በማድረግ (ኳረንቲን) መግባት ቢፈልግ ቫይረሱ ▶**

**ቢኖርበትም ባይኖርበትም ራሱን ከቫይረሱ ነጻ ለማድረግ ምን ምን ማድረግ ይገባዋል?**

አንድ ቫይረሱ እንዳለበት የጠረጠረ ሰው ለሚመለከተው ክፍል በስልክ ማሳወቅና ምርመራ ያስፈልገገው እንደሆን የጤና ባለሙያዎችን ውሳኔ ማወቅ አለበት። ካለን የአኗኗር ዘይቤ አንፃር የቤት ውስጥ ህክምና ፈፅሞ ባይመከርም በአጠቃላይ ግን በሽታው ቀላልና መካከለኛ ደረጃ ከሆነ የሚደረጉ የቤት ውስጥ ክንውኖች ራስን ለሁለት ሳምንት ማግለል፣ አልጋን የመመገቢያ እቃዎችን መለየት፣ በቂ ፈሳሽ መውሰድ፣ በቂ እረፍት ማድረግ፣ የበሽታውን ስሜትና ምልክቶች ለማጥፋት ትኩሳት ራስ ምታት ቁርጥማት ካለ ፖራሲታሞል አይነት ሕመም ማስታገሻ መጠቀም ሳልና የአፍንጫ ፈሳሽ የጉሮሮ መከርከር ካለ ከዚ ቀደም ጉንፋን ሲይዘን የምንጠቀማቸው መዳኒቶች መጠቀም እንችላለን ። ነገር ግን ለባክቴሪያ ኢንፌክሽን የሚሰጡ አንቲባዮቲኮችን ከመውሰድና በተሳሳተ መንገድ ያሽላሉ ተብለው በማህበረሰቡ ዘንድ ከሚነገርላቸው ሰውነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ከሚያመጡ ውህዶችን ከመውሰድ መቆጠብ በሽታው የመሻሻል ሳይሆን የመባባስ ትንፋሽ የማጠር የደረት ሕመም የሰውነትና የከንፈር ከለር ጠቆር ማለት ካለ ወዲያው ሪፖርት አርጎ የሆስፒታል ውስጥ ህክምና መጀመር አለበት፡፡

**በየመንደሩ የሚዘጋጁ የአፍ መሸፈኛ (ጭምብሎች) የመከላከል አቅማቸው ምን ያህል አስተማማኝ ነው? ሙሉ ለሙሉ ትንፋሽን ስለሚገድቡ በጤና ላይ የሚያደርሱት የጤና እክል አይኖርም?**

በጨርቅ የሚሰሩ የአፍ መሸፈኛዎች ስካርፍን ጨምሮ ሰዎች በሚበዙባቸው ቦታዎች ላይ እንድናደርግ የተለያዩ አለም አቀፍ የጤና ድርጅቶች ያዘዙ ሲሆን የሚሰሩበት ግብአት እና ጥራት ስለሚለያይ እንደ ሰርጂካል ማስክና N95 የመከላከል ብቃቱን በቁጥር ለማስቀመጥ የተጠና በቂ ጥናት የለም ። ነገር ግን CDC ያዘዘበት ዋናው ምክንያት ብዙ ሰው በሽታው ኖሮበት ምልክት ላያሳይና ወደ ሌሎች ሰዎች ሊያሰራጭ ስለሚችል ይህን የጨርቅ ማስክ በማድረግ በማውራት በማሳል እንዲሁም በማስነጠስ ወቅት ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው የሚሄደውን ፈሳሽና ቫይረስ(large droplets ) ስለሚያቅብ ጭምብል አድራጊው ሌሎች ሰዎችን እንዲከላከል ታስቦ ነው። እነኚህ የጨርቅ መሸፈኛዎች የአሰራር ስታንንዳርድ ያላቸው ሲሆን በየመንደሩና በየመናኸሪያው



የሚሸጡ የጨርቅ ጭምብሎች እና ሳኒታይዘሮች ምን ያክል ጥራት ያሟሉ ናቸው የሚለውንና ከንክኪ መፅዳታቸውን ጥራትና ደረጃ መዳቢ ባለስልጣን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ጥልቅ ዳሰሳ ሊያደርጉበት ይገባል። እነኚህ የጨርቅ ጭምብሎች ማህበራዊ ፈቀቅታን የማይተኩ ሲሆን ያለ ማህበራዊ ፈቀቅታ እና ሌሎች መከላከያ ዘዴዎች ብቻውን ፋይዳ የለውም። _እነኚህ የጨርቅ ጭምብሎች ትላልቅ ውህዶችን እንደ ፈሳሽ እና ትላልቅ ጀርሞች እንዳይወጡ ቢያቅብም እነደ አየር (ጋዝ) ያሉ ጥቃቅን ንጥረ ነገሮች እንደ ልብ እንዲወጣና እንዲገባ ስለሚያደርጉ በምናደርጋቸቸው ጊዜ ከሚሰማን አለመመቸት ሙቀት እና የፊት መቆጣት ባለፈ የከፋ ተጓዳኝ የአተነፋፈስ የጤና እክል አያስከስቱም።

**የኮሮናን እንቅስቃሴ በአፋጣኝ ለመግታትና ወደ ቀደመ እንቅስቃሴ ለመግባት ምን አይነት ሥራዎች ሊሰሩና ሊተገበሩ ይገባል?**

ከጎረቤት አገራትበሽታው በስፋት እንዳይሰራጭ ድንበሮች አካባቢ ከፍተኛ ህዝብን የማንቃት ስራ,የድንበር ላይ እስክሪኒንግ በሰፊው ማካሄድ ,ድንበር አካባቢ የጉዞ ገደብ መጣል፤_በትንሹ ለ2 ሳምንት የሚቆይ ከቤት ያለመውጣት ገደብ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ተግባራዊ ማድረግና ድንገተኛ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ከክልል ክልል ከከተማ ከተማ እንዲሁም የከተማ ውስጥ እንቅስቃሴዎች በመግታት ስርጭቱን መቀነስ፣_የመመርመር አቅማችንንና የምርመራ ማእከላትን ቁጥር መጨመር_ጥቆማ በሚደረግበት ጊዜ የታካሚው ምልክቶች ከወረርሽኙ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ እና ጤና ባለሙያው ምርመራ እንዲደረግ ከወሰነ ታካሚው ባለበት ቦታ የላብራቶሪ ባለሙያው ሄዶ ናሙና የሚወስድበት ሲስተም በመዘርጋት ታካሚው ከቦታ ቦታ በማዘዋወር ሂደት ውስጥ የሚከሰትን ስርጭት መግታት የየእለት ሪፖርቱ ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ መስጠት በተለይም ታካሚው የመጣበት ከተማ ብቻ ሳይሆን ከየት መንደር እንደሆነ ለማህበረሰቡ በግልፅ ማሳወቅ ስርጭቱን በቦታ ማፕ ለማድረግና ማህበረሠቡም ጥንቃቄ እንዲያደርግ ይረዳል፡፡ የየቀን የታማሚዎችን ቁጥር ሪፖርት ከማድረግ በዘለለ በአገር አቀፍ ደረጃ ጥናቶች እንዲደረጉና አለም አቀፍም ሆነ አገር አቀፍ የጥናት ውጤቶችን ህዝቡ እንዲደርሰው በየመገናኛ ብዙሃን ማሰራጨት

**ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ኢትዮጵያ ከሌሎች ወረርሽኙን ከተቆጣጠሩት ሀገራት የምትወስደው ተሞክሮ ይኖር ይሆን? ካለ ቢጠቅሱልን፡፡**

ችግሩን ቀድመው ተረድተውና አፋጣኝ እርምጃ ከወሰዱ እንደነ ቻይና ካሉ አገራት ምንወስደው ተሞክሮ ማህበረሰባችንየጤና ባለሙያን ምክር መስማትና ለህግ መገዛት ያለውን ጥቅም ሲሆን መንግስትም ቁርጠኛ አቋም መያዝና ህግን የማስፈፀምን ብቃት ህዝብን ምን ያክል ከእልቂት የሚታደግ መሆኑን ነው። _የችግሩን ጥልቀት ካለመገንዘብና ከመዘናጋት ዋጋ ከከፈሉና ከባድ ኪሳራ ካስተናገዱት የአውሮፖ አገራትና አሜሪካም ብዙ ትምህርት መውሰድ አለብን።

**ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ኮሮናን ከመከላከል አንፃር ምን አይነት ሚና ሊኖራቸው ይገባል?**

በህዝብ ዘንድ ካላቸው ተደማጭነት እና ተቀባይነት አንፃር እንዲሁም ለህዝብ ጥቅም እንደመቆማቸው የተለያዩ አደረጃጀቶቻቸውን ተጠቅመው ህዝቡን ማስተማር ማንቃት፣ የበጎ አድራጎት ስራዎችን መስራት፣ ህዝቡ እንዲረዳዳ ጥሪ ማቅረብ፤, የፖለቲካ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ወረርሽኙን ለመመከት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ከመንግስት ጎን መቆም፣ ይህን አለም አቀፍ ወረርሽኝ እና ግርግር ተጠቅሞ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ከሚደረግ እንቅስቃሴ ተቆጥበው እንደሰለጠነ እና ለህዝብ አደራ እንደተቀበለ ተቋም ለህዝብ በሚጠቅሙ አካሄዶች ላይ ብቻ ሊንቀሳቀሱ ይገባቸዋል።

**በጥያቄዎቻችን ላይ መነሳት ሲኖርባቸው ያላነሳናቸው ጥያቄዎች ካሉና በእርስዎ በኩል የሚጨምሩት አስተያየት ካለ?**

በሽታው አዲስ ስለሆነ እና ገና ብዙ ጥናቶች እየተደረጉ ስለሆነ እለት እለት አዳዲስ ግኝቶች እየተገኙ ስለሆነ ስለቫይረሱ በእርግጠኝነት መናገር ያዳግታል ለዛም ነው የአለም አቀፍ ጤና ድርጅቶች ትእዛዝና ምልከታ ቶሎ ቶሎ የሚቀያየረውና መድሃኒትም ሆነ ክትባት እስካሁን ያልተገኘው። አንድ ነገር ላይ ግን እርግጠኛ ነን፡፡ በመከላከል ከወረርሽኙ እልቂት መትረፍ እንደምንችል፤ ስለዚህ ባለን አንድ መፍትሄ ላይ ባንቀልድ እላለሁ።





# “ብልፅግና ፓርቲ የኮሮና ቫይረስን ለፖለቲካ መጠቀሚያ እያደረገው ነው።”

ዋሲሁን ተስፋዬ

ግንቦት 8 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ብልፅግና የኮሮና ቫይረስን ለፖለቲካ መጠቀሚያ እያደረገው ነው ሲሉ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

የኢዜማ አባላት በየትኛውም አካባቢ ሁለትና ሶስት ሰው ሆነው መንቀሳቀስ አለመቻላቸውን ኮሮናን ለመከላከል በሚደረጉ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን መሥራት እንዳይችሉ ከፍተኛ እንቅፋት እያጋጠማቸው እንደሆነ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡ እንቅፋት እየገጠማቸው ካሉት አካባቢዎች መሀልም ሀዲያ፣ ሾኔ፣ ቦዲቲ፣ ወላይታን በምሳሌነት ጠቅሰዋል፡፡ እንደ ኃላፊው ገለፃ የብልፅግና ፓርቲ አንድ ለአስር የሚል አሰራር ዘርግቶ ሕዝቡን እየሰበሰቡ የፖለቲካ ሥራ እየከወኑ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

የብልፅግና አመራሮች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ላይ ከአራት ሰው በላይ መሰብሰብ አይችልም የሚለውን አዋጅ በመጣስ በወረዳና በዞን ደረጃ የሚያካሂዱትን ስብሰባ አላቆሙም፤ በየቦታው ከ50 እና 60 በላይ ሰዎችን እንደሚሰበስቡ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ሰውን በመሰብሰብ ዓለም አቀፍ ስጋት ስለሆነው ኮሮና ከማስተማርና ግንዛቤ ከማስጨበጥ ይልቅ ስለ ቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫ እንደሚወያዩ ለማወቅ መቻላቸውን ኃላፊው ያነሳሉ፡፡ የብልፅግና ፓርቲ በኮሮና ምክንያት ድጋፍ ለማድረግ ከህብረተሰቡ የሚሰበስቡትን ንብረቶችንና የድጋፍ እቃዎችን በብልፅግና ስም እያደለ ህግን የጣሰ አሰራር እየተከተለ እንዳለ የሚገልፁት ኃላፊው፣ የኢዜማ አባሎችና አመራሮች ግን በየቦታው መንቀሳቀስ አለመቻላቸውን በተለይ በኦሮሚያ ክልል ህብረተሰቡን በማስተባበር የደም ልገሳ ያደረጉ የኢዜማ ሥራ አስፈጻሚዎች መታሰራቸው እንዳሳዘናቸውና ብልፅግና በፊት ኢሕአዴግ ሲጓዝበት በነበረው አካሄድ እየሄደ እንዳለና ይሄ አካሄድ የትም እንደማያደርሰው በመገንዘብ አሁን ያለው አመራር ይሄን መፍትሔ ሊሰጥበት ይገባል ሲሉ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ብልፅግና ፓርቲ ከኮሮና ቫይረስ ጋር ተያይዞ የሚሰራቸው የበጎ አድራጎት ሥራዎች ለፓርቲው ገጽታ ግንባታ እያዋለው ነው በሚል ከሌሎች ፓርቲዎችም ትችት ሲቀርብበት እንደነበር ይታወሳል፡፡

# "ከሁሉም ህብረተሰብ ክፍል የሚበቃ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል አለ ብለን አናምንም"

ሙሉዓለም ተገኝ ወርቅ (ዶ/ር)

ግንቦት 8 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



[illegible] አቋቁሞ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በሚገኙ የኢዜማ መዋቅሮች ደም በመለገስ በተሳካ ሁኔታ የመጀመሪውን ሥራ ማጠናቀቁ የሚታወስ ነው፡፡ በቀጣይነትም ህብረተሰቡ መዘናጋቱን ትቶ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች ለመስራት፣ በመንግስት በኩል ያሉ ክፍተቶች እንዲታረሙ ለማድረግ የታዩ ክፍተቶችን የመለየት ሥራ ግብረ ኃይሉ እየሰራ እንደሚቀጥል ግብረ ኃይሉ ለዜጎች መድረክ ገልጿል፡፡

ከሰሞኑ የፀጥታ አካላት የአፍ መሸፈኛ ጭምብል ማድረግ ግዴታ መሆኑን በመግለጽ እርምጃ እየወሰዱ መሆኑን በማስመልከት በዚህ ላይ ምላሻቸውን እንዲሰጡ የዜጎች መድረክ የኢዜማ የኮሮና ቫይረስ ግብረ ኃይል አስተባባሪ ሙሉዓለም ተገኝ ወርቅ (ዶ/ር) የጠየቃቸው ሲሆን ዶ/ሩም "የአፍ መሸፈኛ ጭምብል ለሁሉም ህብረተሰብ የሚበቃ አለ ብለን አናምንም፡፡ እንደ ሀገር የተሰጠ መመሪያ ስለሌለ አግባብ አይደለም፡፡ ማንኛውም ሰው የአፍ መሸፈኛ ያድርግ የሚል መመሪያ የለም፡፡ እርምጃው በተናጥል እየተወሰደ ስለሆነ ወጥ የሆነ አሰራር መኖር አለበት" ብለዋል፡፡

የዓለም አቀፉ የጤና ድርጅት (WHO) ኮሮና [illegible] አይጠፋም በማለት የጤና ድርጅቱ አሳውቋል፡፡ እንደ ሀገር ጥናት መደረግ አለበት፡፡ እኛም አንደኛ ያየነው ክፍተት ይሄን ነው፡፡ በቫይረሱ በምን አይነት የእድሜ ክልል ላይ ያለን ሰው ነው እየያዘ ያለው? ምን አይነት አካባቢ ነው እየታየ ያለው? የሚለውን የሚያጣራ እንደ እኛ ህብረተሰባችን ተጨባጭ ሁኔታ ጥናቶች መደረግ አለባቸው፡፡ በአለም ላይ ብዙ እስካሁን ያልጠፉ ቫይረሶች አሉ፡፡ ኮሮና አይጠፋም ካልን በቀጣይ ምንድን ነው የምንወስደው እርምጃ፣ ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን? የሚሉ ምላሾች መኖር አለባቸው፡፡ ምላሾች ሳይኖረን እርግጠኛ ሳንሆን መናገር የለብንም፡፡" በማለት ገልጸዋል፡፡

ኢዜማ ህብረተሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ፣ ለሥራውም የተለያዩ ፖስተሮች እንዳሳተመ፤ በማኅበራዊ ሚዲያም "አንዘናጋ እንጠንቀቅ!" የሚሉ መልእክቶችን እያስተላለፈ የሚገኝ ሲሆን በቀጣይም በእያንዳንዱ ወረዳ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ላይ ፓርቲው እንደሚሳተፍ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ ያስረዳል፡፡

# በኦሮሚያ ክልል ባሌ ጎባ ምርጫ የሚገኙ የኢዜማ ሥራ አስፈጻሚ አባላት ታሰሩ

ግንቦት 8 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በኦሮሚያ ክልል ባሌ ጎባ ዞን ምርጫ ወረዳ ያሉ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ከቅዳሜ ግንቦት 1 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ያለ አግባብ መታሰራቸውን፤ ህጉ በሚያዘው መሠረት ፍርድ ቤት መቅረብ አለመቻላቸውን ታወቀ፡፡

ኢዜማ የአባሎቹን መታሰር ጉዳይ ትኩረት በመስጠት ሂደቱን በመከታተል አባላቶቹ ያለአግባብ ስለታሰሩ እንዲፈቱ መንግስትን በተደጋጋሚ ቢጠይቅም ሊፈቱ እንዳልቻሉ የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ገልፀዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል የታሰሩት የኢዜማ ሥራ አስፈጻሚዎች በኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የፓርቲውን ሥራ አቁመው ወረርሽኙን ለመከላከል በሚረዱ በበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ በመሳተፍ በአካባቢው ካለው ደም ባንክ ጋር በመነጋገር አባላቶቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን አስተባብረው ደም ለመለገስ የቻሉ ሲሆን ከደም ልገሳው ጋር ተያይዞ፡- "ህጋዊ እውቅና ሳይኖራችሁ እኛን ሳታስፈቅዱ ደም ለግሳችኋል፤ ደም መለገስ ለምን አስፈለገ? በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ፎቶ ለጥፋችኋል" በሚል ምክንያት ሥራ አስፈጻሚዎቹን ካሰሩ በኋላ ታሳሪዎቹ በሌሉበት ቤታቸውን በመፈተሽ የኢዜማን አርማ፣ የፓርቲውን ሰነድና ፎርሞች፣ የአባላት መመዝገቢያ ቅጽ፣ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እንደተወሰደባቸው ህጉ በሚያዘው መሠረት ፍርድ ቤት ሊቀርቡ እንዳልቻሉ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው አስረድተዋል፡፡

ግንቦት 01 ቀን 2012 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ በቁጥጥር ስር የዋሉት ሥራ አስፈጻሚዎች ግንቦት 5 ቀን 2012 ዓ.ም ጎባ ወረዳ ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ፖሊስ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ጠይቆባቸው ፍ/ቤቱ ለግንቦት 10 ቀን 2012 ዓ.ም ቀጠሮ እንደሰጣባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡